የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፬ ቀን ፳፻፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 13
ADDIS ABABA, 14th December, 2015

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፷፩/፳፻፰ ዓ.ም

የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………ገጽ ፰ሺ፮፻፹፩
አባሪ……………………………………….ገጽ ፰ሺ፮፻፹፫

CONTENTS

Regulation No.361/2015

Rate of Fees for Seed Competency and Related Services Council of Ministers Regulation…………… ……………………….………. …….Page 8681
Annex…………………………………….Page 8683

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፩/፳፻፰

የዕጽዋት ዘር የብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን የክፍያ ተመን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፳፻፰ አንቀጽ ፭፣ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፲፱፻፺፩ አንቀጽ ፲፯ (፩) እና በዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፪/፳፻፭ አንቀጽ ፳፯ (፩) መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ
ይህ ደንብ "የዕጽዋት ዘር ብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶችን ክፍያ ተመን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፩/፳፻፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ
የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦
፩/ "አዋጅ" ማለት የዕጽዋት ዘር አዋጅ ቁጥር ፯፻፹፪/፳፻፭ ነው፤

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 361/2015

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE THE RATE OF FEE FOR SEED COMPETENCY AND RELATED SERVICES

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015, Article 17(1) of the Federal Government of Ethiopia Financial Administration Proclamation No. 648/2009 and Article 27(1) of Seed Proclamation No. 782/2013.

1. Short Title
This Regulation may be cited as the "Rate of Fees for Seed Competency and Related Services Council of Ministers Regulation No. 361/2015".

2. Definition
In this Regulation unless the context otherwise requires:
1/ "Proclamation" means the Seed Proclamation No.782/2013;

፪/ በአዋጁ ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፫. <u>ስለአገልግሎት ክፍያ</u>

የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአዋጁ በተደነገገው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ በተመለከተው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

፬. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሣለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ definitions provided for under the Proclamation shall be applicable.

3. <u>Service Fees</u>

Service fees shall be payable for services rendered by the Ministry of Agriculture and Natural Resources in accordance with the Proclamation at the rate prescribed in the schedule attached herewith.

4. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 14th day of December, 2015.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የዕጽዋት ዘር የብቃት ማረጋገጫና የተያያዥ አገልግሎቶች የክፍያ ተመን ሠንጠረዥ

የአገልግሎት ዓይነት		የክፍያ መጠን (በብር)
ለማመልከቻ ምርመራ	ለዘር ንግድ ምዝገባ	100.00
	ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ	100.00
	ለግዴታ ፍቃድ	100.00
	ለብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ ሙከራ	100.00
	ለዘር መስክ ቁጥጥር	100.00
	ለላቦራቶሪ ሙከራ	100.00
የዘር ምርመራ	ለብቅለት	40/ናሙና
	ለተትራዞልየም	47/ናሙና
	ለንህጽና	20/ናሙና
	ለእርጥበት	25/ናሙና
	ለጤና	182/ናሙና
የመስክ ቁጥጥር	ለድቃይ በቆሎ	30/ሄክታር
	ለሌሎች ሰብሎች	20/ሄክታር
ናሙና ለመውሰድ	ለሁሉም ሰብሎች	20/ናሙና
የምስክር ወረቀት	ለጸደቀ ዘር	100.00
	ጥራቱ የተገለጸ ዘር	100.00
	ለዘር ላቦራቶሪ ሙከራ	100.00
	ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ ሙከራ	100.00
	ለዝርያ ምዝገባ	100.00
	ለብቃት ማረጋገጫ	100.00
	የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀት ለመቀየር	100.00
	ለዓመታዊ ክፍያ	200.00
የዝሪያ ሙከራ	ከሌላው የተለየ፣ ወጥነት ያለው እና ሊቀያየር የማይችል የዝርያ ባህሪ (ዝርያ በቁጥር እና በወቅት)	4,000.00
	ለብሔራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ (በዝርያ፣ በወቅት እና በቦታ)	11,000.00

SCHEDULE OF RATE OF FEE FOR SEED COMPETENCY AND RELATED SERVICES

Types of Service		Amount of Fee (Birr)
Examination of Application for:	Registration of seed business	100.00
	Distinctness, Uniformity and Stability Testing	100.00
	Compulsory Certificate	100.00
	National Performance Trial	100.00
	Field Seed Inspection	100.00
	Laboratory Test	100.00
Seed Test for:	Germination	40/ sample
	Tetrazolium	47/ sample
	Purity	20/ sample
	Moisture	25/ sample
	Health	182/sample
Field inspection for:	Hybrid maize	30/hectare
	Other crops	20/hectare
Sample Collection:	for all crops	20/sample
Issuance of Certificate for:	Approved Seed	100.00
	Quality Declared Seed	100.00
	Laboratory Test Result	100.00
	Distinctness, Uniformity and Stability Testing Result	100.00
	Variety Registration	100.00
	Assurance Competance	100.00
	Replacement of lost or destroy certificate	100.00
	Annual fee	200.00
Variety Trial for:	Distinctness, Uniformity and Stability (per number of variety and season)	4,000.00
	National Performance (per variety, season and site)	11,000.00